የአውሮፓና የአፍሪካ የቅንጅት የድጋፍ ድርጅቶች ምክር ቤት
The Council of Europe and Africa Kinijit Support Groups
1 Crowndale Road London NW1 1TU UK Tel: +44 (0) 20 7168 9893 Email: euafkinijit@googlemail.com

# የአዉሮፓና የአፍሪካ የቅንጅት ድጋፍ ድርጅቶች ምክር ቤት መቋቋምን አስመልክቶ የተሰጠ መግለጫ

## ለአሰተማማኝ ድል፤ የተቀናጀ ትግል!!!

በሀገራችን ፈንጥቆ የነበረዉና በምርጫ 97 ማህተም የታተመበት የዴሞክራሲ ጭላንጭል በወያኔ አምባገነናዊ ለህዝብ ድምጽ አልገዛም ባይነት ከተቀለበሰ ወዲህ በኢትዮጵያ ውስጥ የተለዩ የፓለቲከ አመለካከት ይዞ በተቃዋሚነት መንቀሳቀስ የሚያሳስርና የሚያስገድል ትልቅ ወንጀል ሆኗል:: ስለ ዴሞክራሲ፤ ፍትህና ሰብአዊ መብት መከበር የሚያላዝነዉ የትግራይ ነጻ አዉጭ ድርጅት በምርጫ 97 በህዝብ መተፋቱን ከተረዳ ወዲህ ያጠለቃትን የይስሙላ ጭንብል አዉልቆ ጥሎ፤ የተለየ አመለካከት ያለዉን ሁሉ እንደ ደበኛ ጠላት በመቁጥር፤ ጠመንጃዉን ወድሮ፤ የፓሊስና የጸጥታ መረቡን አጠናክሮ፤ ከተቆናጠጠበት የሥልጣን ማማ ላለመዉረድ ህዝብን በሃይማኖት፣ በጎሳና በቋንቋ እየመነዘረ በመከፋፈል ላይ የተመሰረተ የአፈና አገዛዙን አጠናክሮ ቀጥሎበታል::

የዴሞክራሲያዊ ሥርዓትና የመልከም አስተዳደር መግለጫ የሆኑ መሰረታዊ የዴሞክራሲ መርሆዎችን በመጣስና መንግስታዊ ተቋማትን የሥርዓቱ መጠቀሚያ በማድረግ የዜጎችን ፓለቲከዊና ሰብአዊ መብቶች በማንአለብኝነት በመርገጥ ላይ ይገኛል:: ወያኔ በኢትዮጵያ የዴሞክራሲና የመልከም አስተዳደር ግንባታ ሂደት ላይ የፈጸመዉ ደባና ግፍ እንዲህ በቀላሉ የሚገመት አይደለም:: ማቆጥቆጥ ጀምሮ የነበረዉና የህዝብ ልሳን የሆነዉ የነጻዉ ፕሬስ ግብአቶች ሙሉ በሙሉ ተዘግቷል:: በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸዉ ተቃዋሚ የፓለቲካ ድርጅቶች ማዕቀብ ተጥሎባቸዉ ፍጹም ዘረኛነት በተላበሰ ሁኔታ የአንድ ጠባብ ቡድን የበላይነት ሰፍኖ ይታያል::

ከሁሉም በላይ በሰላማዊና ሕጋዊ መንገድ በሚታገለዉ፤ለዲሞክራሲዊና ለሰብአዊ መብቶች መከበር ፍጹም ታማኝና የህዝብን ፍቅርና ታአማኒነት አግኝቶ ዉክልና በተሰጠዉ በቅንጅት ለአንድነትና ለዴሞክራሲ ላይ ያደረሰዉ በደል በቀላሉ የሚገለጽ አይደለም:: ቅንጅት ለሰላም የቆመ ድርጅት መሆኑ ቢታወቅም፤ በአመጽ ተወልዶ በሽብር የሚኖረዉ ዘረኛዉ ወያኔ በፈጸመበት ፋሺስታዊ ጥቃት በሀገር ዉስጥ እንቅስቃሴዉ ከተገታ ሁለተኛ ዓመቱን ሊይዝ ነዉ:: ቅንጅት የከፈታቸዉ ቢሮዎች ቁልፎቻቸዉ እየተሰበሩና ዉስጣዊ ድርጅታቸዉ እየተበረበረ ሰነዶችና ንብረቱ ተዘርፎ እንዳይንቀሳቀስ ተደርጎአል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ብርቅዬ ልጆች፤ የሰላም ፋና ወጊዎችና የዴሞክራሲያ ሐዋርያት የሆኑት የቅንጅት መሪዎቹ በሀሰት የተዘጋጀ የዘር ማጥፋትና የሀገር ክህደት ወንጀል ክስ ተመስርቶባቸዉ፤ተጋዳላይ ካድሪዎች በዳኝነት በተሰየሙበትና በወረት የተገዙ ምንደኞች በምስክርነት በሚቀርቡበት የፍርድ አደባባይ እየተጉላሉ የፍትህ ቁማር ጨዋታ ከተጀመረ ከአንድ ዓማት በላይ ሆኗል::

የዚህ አይነቱ አስገዳጅ ሁኔታ መፈጠር ከነባራዊ ሁኔታዉ ጋር የሚጣጣም ወቅታዊ የትግል ስልትና ስትራቴጂ መንደፍ ግድ ብሎአል:: የአንድ ድርጅት የትግል ስልት በጊዜ፤በቦታና በሁኔታ ይወሰናል:: በመሆኑም የቅንጅት መሪዎች በመታሰራቸዉና ድርጅቱም እንደ ወንጀለኛ ተቆጥሮ እንዳይንቀሳቀስ በመደረጉ የተፈጠረዉን የአመራር ክፍተት ለመሙላት የቅንጅት ዓለም-አቀፍ የፓለቲከ ኮሚቴ እንዲመሰረት ተድርጎአል::

ቅንጅት ዓለም-አቀፍ ከተመስረተ ካለፈዉ አንድ ዓመት ወዲህ ፓለቲካዊና ድርጅታዊ እንቅስቃሴዎችን በማድረግ የቅንጅት ራእይና የትግል መንፈስ እንዲቀጥል አድርጓል:: ከዚህ አኳያ በተለያዩ አህጉራት የቅንጅት ድጋፍ ከሚቴዎች እንዲዋቀሩ ያደረገዉ አስተዋጽኦ የላቀ ድርሻ ሲኖረዉ በዚህም በኩል በተደረገዉ ጥረት ዛሬ ብዙ ኢትዮጵያዉያኖች በሚኖሩባቸዉ አገሮችና ከፍለ-አህጉሮች ደጋፊ ሃይላት ተደራጅተዉ በመንቀሳቀስ ላይ ናቸዉ::

እኛም በአዉሮፓና በአፍሪከ አህጉራት በራሳችን አነሳሽነት ተቋቋምን የቅንጅትን ዓላማ ስናራምድ የቆየን የድጋፍ አስተባባሪ ድርጅቶች ቅንጅት ይዞት የተነሳዉ ሕዝብን ከግፍ አገዛዝ ነጻ የማዉጣት ዓላማ ግቡ እንዲመታ በጋራና በተናጠል የቻልነዉን ያህል ጥረት ስናደረግ ቆይተናል:: ሆኖም ግን አሁን አገራችን ከለችበት አስቸጋሪ የፓለቲካ፤ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ኑሮ ቀዉስ፤ እንዲሁም

ትግሉ ከሚጠይቀዉ መስዋእትነት አኳያ የተባባረና የተቀነባበረ ትግል ማድረግ የተሻለ አማራጭ መሆኑን ተገንዝበናል። በመሆኑን «ለአስተማማኝ ድል፤የተቀናጀ ትግል» በሚል መሰረታዊ መርህ ላይ በመመርኮዝ፤ ከብዙ ዉጣ-ዉረድ በኋላ ለረጅም ጊዜ በጉጉት ሲጠበቅ የነበረዉ ምኞት ተሳክቶ አባል ድርጅቶች ኤፕሪል 1 ቀን 2007 ባደረጉት የጋራ ስብሰባ የመተዳደሪያ ደንቡን በማጽደቅ የጋራ መድረክ ፈጥረዋል። በዚህም መሠረት፤

1. ከዘጠኝ የአዉሮፓ አገሮችና ከደቡብ አፍሪከ የቅንጅት ድጋፍ ድርጅቶች የተወከሉ አባላትንና የኦስትራሊያን ቻፕተር በክብር አባልነት ያቀፈ «የቅንጅት የአዉሮፓና የአፍሪካ የጋራ ምክር ቤት» ተቋቁሟል።

2. የምክር ቤቱን ተግባርና አጠቃላይ እንቅስቃሴ የሚያስተባብርና በማዕከልነት የሚያገለግል አንድ ሴክሬታሪያት በእንግሊዝ አገር፤ ለንደን ላይ እንዲቋቋም ተወስኗል። ሁለት የጽህፈት ቤት ሃላፊችንም መድቧል።

3. ምክር ቤቱን በበላይነት የሚመራና የሴክሬታሪያቱን ተግባራዊ እንቀስቃሴ የሚቆጣጠር 16 አባላት ያሉት የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተሰይሟል። የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴዉን ለሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት በሊቀመንበርነት እንዲመሩ ከሰዊስ ቻፕተር አቶ ምስጢረ ኃይለስላሴ በጋራ ስምምነት (በኮንሴንሰስ) ተመርጠዋል። ምክር ቤቱ የተጣለበትን ከባድ ሃላፊነት ለመወጣት በሚያደርገዉ ዘርፈ-ብዙ እንቅስቃሴ አሳታፊነትንና ተሳትፎን በመቀበል በሥሩ የተለያዩ የዘርፍ አስተባባሪ ኮሚቴዎች ሲኖሩት፣ በቅርቡ የኦዲት ኮሚሽንና እንደ አስፈላጊነቱም ሌሎች የተግባር ቡድኖችን የሚያቋቁም ይሆናል።

4. ምክር ቤቱ የትግል አጋርነታቸዉን በመግለጽ የድጋፍ መልዕክት ላስተላለፉለት ለቅንጅት ዓለም-አቀፍና ለሰሜን አሜሪካ የቅንጅት ድጋፍ አስተባባሪ ድርጅትና ለሌሎችም እህት ድርጅቶች ምስጋና እያቀረበና አድናቆቱን እየገለጸ፤ ለጋራ ዓላማ መሳካት በሚደረገዉ የጋራ ትግል በአጋርነት እንደሚቆም ያረጋግጣል።

5. ምክር ቤቱ ቅንጅት የኢትዮጵያን ሕዝብ ከወያኔ ዘረኛ አምባገነናዊ አገዛዝ ነጻ ለማዉጣት የጀመረዉን ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ ትግል ከግብ ለማድረስ የበኩሉን አስተዋጽኦ ለመወጣት በጽናት እንደሚቆም እያረጋገጠ ለሀገርና ለወገን ተቆርቋሪ የሆኑ ሃይሎች ሁሉ ከጎኑ እንዲቆሙ ጥሪዉን ያቀርባል።

ኤፕሪል 1 ቀን 2007